# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው - ሕዝብ
(ወዛደር፤ ገበሬ፤ ነጋዴ፤ ወታደር፤ ምሁር፤)
መብትና ጥቅም
የሚታገል ጋዜጣ

መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)
All ETHIOPIA SOCIALIST MOVEMENT (ME'ISONE)
P. O. Box 3198 . 10364 Stockholm 3 . Sweden . e-mail: meisone@t-online.de

| ዓመት 29 | ቁጥር 1 መስከረም 1995 |
|---|---|


# ብሄራዊ ዕርቅ ስንል

"ብሄራዊ ዕርቅ" የሚለው ቃል የኢትዮጵያን ተጠባጭ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሁኔታ ከማገናዘብ ጋራ በተያያዘ መነሳት ከጀመረ ቢያንስ የወያኔ ሥርዓት በኢትዮጵያ ምድር ካስቆጠረው ዕድሜ ጋር እኩል ነው። ጥያቄው የሚነሳውም በስልጣን ላይ ካለው የገዢ ሃይል ጋር በተቃውሞ በቆሙ የፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆን፣ ባጠቃላይ የሃገሪቱ ሁኔታ በሚያሳስባቸው ዜጎች ጭምር ነው። የጉዳዩም መሰረታዊ መነሻ ተወደደም ተጠላ የአንድ ከህብረተ ሰቡ ባጣም አናሳ ከሆነው የጎሳ ክፍል የመጣ ሃይል በጠመንጃ እየታገዘ ህብረተሰቡን በጎሳ ከፋፍሎ በአብላጩ ህዝብ ላይ ያሰፈነው የፈላጭ ቆራጭ አጋዛዝ ሲሆን፣ ሁኔታው ብዙ መመሰቃቀሎችን ፈጥሮ፣ ሃገሪቱን በተረጋጋና በሰከነ መንፈስ ወደልማትና ዕድገት መምራት ካለማስቻሉም በላይ፣ ስርዓቱ ከቀን ወደቀን ወደሌላ የከፋ ጥፋት ሊያመሩ የሚችሉ ግችቶችና ትርምሶችን እየወለደና እያሰተናገደ፣ ከጠቅላላው ህብረ ተሰብ ጋር በመላተም አገዛዙና ህብረተ ሰቡ ሆድና ጀርባ ስለሆኑ፣ ሃገሪቱ በሁለት የተቃቃሩ ሃይሎች መካከል የምትዋዥቅ፣ ከልማቷ ይልቅ ጥፋቷን የሚያፋጥን ብሄራዊ ትርምስ ውስጥ ስለተከተተችና ከዚህ ብሄራዊ ትርምስ ለመውጣትም ብሄራዊ መፍትሄ ከመሻት ያነሰ ሊወሰድ የሚችል አማራጩ ስለማይኖር፣ ስለዚሁ የመፍትሄ ሃሳብ ያለንን ግነዛቤ እንቃኝ፣

በየትኛውም ደረጃና በማንኛውም መልክ ብሄራዊ ተብሎ ለሚፈረጅ ሃገራዊ ችግር መፍትሄ አሰጣጥ ከሁሉም አስቀድሞ የሚጠይቀው የብሄራዊ ሃይላትን ትብብርና እነደ አንድ ሰው ሆኖ መነሳትን መሆኑ አከራካሪ አይደለም።

ስለሆነም ነው ታዲያ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የሰፈኑት ዓይነታቸው የበዛ ቀውሶች ምንጫቸው መጥፎ ፖለቲካዊ አስተዳደር የሆነውን ያህልና አጠቃላይ ህብረተሰቡን የነካ በመሆኑ፣ ሁኔታውን ለማረም የብሄራዊ መፍትሄን የሚሹ ወገኖች ብሄራዊ እርቅ የሚለውን መፈክር አንስተው የሚንቀሳቀሱት።

ቀደም ሲል በሃገሪቱ ፣ ህዝብና ሥርዓቱ ሆድና ጀርባ መሆናቸውን በጠቆምነው መነሻነት፣ የብሄራዊው እርቅ ጥያቄ ሲነሳ የሥርዓቱ አዛዥ አናዛዥ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ " እርቅ የሚጠየቀው የተጣላ ሲኖር ነው ማን ከማን ተጣላና ነው የእርቅ ድርድር ጉዳይ የሚነሳው "ይህቺ ሁሉ ተፍ-ተፍ ያዴን ሸንኮር ለመመንተፍ" እንዲሉ (የአባባሏ ታሪክ እንዲህ ነው። ከአንድ ትምህርት ቤት በራፍ ላይ ቁጭ ብለው ሸንኮራ አገዳ የሚሸጡ በተለምዶ ልጆች አዴ እያሉ የሚጠሯቸው ሮጊት ነበሩ። ታዲያ አንድ ቀን ተማሪዎቹ ለእረፍት ወጥተው አሮጊቷን ከብበው እማማ አዴ በማለት አንዱ በጀርባቸው ሌላው በጎናቸው ሶስተኛው ከፊታቸው ሆነው እየተንጫጩ ግራ በማጋባት ሸንኮራ አገዳ ለመዝረፍ ያላቸውን እቅድ የተረዳ አንዱ ተማሪ አዬ አሁን ይሄ ሁሉ ተፍ-ተፍ ያዴን ሸንኮር ለመመንተፍ" አለ ይባላል።)ባቋራጭ ስልጣን ለመያዝ የፈለጉ ናቸው የብሄራዊ እርቅ የሚሉ በሚል ጥያቄ ውን ይሸፍኑታል። መቼም ጥል/ጠብ ሲባል ዓይነቱ ብዙ ነው። በጥይት የተጣበሰም፣ በዱላ የተፈናከተም፣ በጩቤ የተዘላዘለም፣ የተሰዳደበበም፣... ወዘተ ዝርዝሩ ተመዝዞ አያልቅምና በኢትዮጵያችን ሁኔታ የተጣላ የለም የሚለውን ለመቀበል ቢያንስ የዚያች አገር ተወላጅ አለመሆንን የሚጠይቅ ይመስለናል። ከዚህ ይልቅ፣ ምናልባት ብለን፣ ሰዎች መጣላትን ወይም ጠብን ካላቸው የህይወት ልምድ ተነስተው ከሚሰጡት የየራሳቸው ትርጉም አቅጣጫ እንመልከተው ቢባልና ከዚያ ተነስተን ብንንዝበት የተሻለ ይመስለናል።

እንዲህ እንጀመር እስቲ፣ ክቡር አቶ መለስን እንደምናውቃቸው ትምህርታቸውን አቋርጠው፣ ጫካ ገብተው፣ ጠብመንጃ ነክሰው /አስነክሰው 17 ዓመት ሙሉ ኤርትራን ከኢትዮጵያ የኮሎንያልዝም ቀንበር ለማላቀቅ ከኮሎኒያልስቱ ጦር ጋር ሲጠዛጠዙ ነው ጠብን የሚያቁት፣ ለሳቸው ጠብ ማለት ያ ቢሆንና፣ "ያላዩት አገር አይናፍቅም" እንዲሉ፣ የተጣላ የለም ሲሉም ፣ ጠብን በዚሁ የጦርነት ህይወት ልምዳቸው መስፈርት ገምግመውት ከሆነ፣ ዕውነታቸውን ብንል በጊዜያዊነት ለመግባቢያነት ሳይረዳ ይቀራል?

አንዳንዴም የቀልድ ወይ የምራቸው ይሁን አይታወቅም እንጂ "ጠንካራ ተቃዋሚ እንፈልጋለን" ሲሉ ይደመጣሉ። ህያው ሆነው ከሚጠቀሱት የክቡርነታቸውና ሌሎቹም ዛሬ ቀን የጎደለባቸው አኒጋቾ ቻቸው የነበሩት ያሏቸውን፣ እንደ "ጦርነት ከፈለጋችሁ መንገዱን ጨርቅ ያድርግላ ችሁ፣ ጦርነትን መዋጋት ብቻ ሳይሆን መስራትንም እናቅበታለን" የሚሏቸውን አባባሎች ብንጠቅስ፣ ጠንካራ ተቃዋሚ ሲሉ ምን ማለታቸው እንደሆነ የግልጽ ግልጽ ነው። ይህ ጠንካራ ተቃዋሚ ሊሆን የሚችለው ለአብዮታዊ ዴሞክራሲ መርሃ ግብር በአማራጭነት በወረቀት አስፍሮ፣ ጠርዞ ከሚያቀረበው ፕሮግራም ባሻገር አንድ በጀርባው የሚታከከው ጠመንጃ ያለው፣ ወይም ደግሞ መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ የተባሉና ጫካ የገቡ አማጽያን፣ ሳይሆኑ በቃኝ አሻፈረኝ፣ አልታዘዝም በማለት፣ ለመግደል ሳይሆን ለመሞት ቆርጠ በተነሳ ሕዝብ ማለትም ጠመንጃ ሳይታከክም፣ ከቅርቡ ትዝታችን የኢንዶኔዥያውን ሱሃርቶ፣ የዩጎዝላቪያውን ሚሎዞቪቺን ከየተኮሰፉበት ዙፋን እያወረደ የከሰካቸውን ሃይል ጭምርም ማለታቸው እንደሆነ ግልጽ ነው። ይህንን በዚሁ ለሳቸውና ለእነሱ እንተውና፣ እኛ ብሄራዊ ጠብ አለ። ይህ ብሄራዊ ጠብ ደግሞ በብሄራዊ ዕርቅ መፍትሄ ማግኘት አለበት የምንልበትን ምክንያታዊ ትንታኔ እንቀጥል፣

የጠቡ መነሾ፡- የተዘረጋው የጎሳ ስርዓት ሁሉም ለሰፈረባት አካባቢ ብቻ እንዲያስብ፣ ከአንዱ አካባቢ ወደሌላው አካባቢ ተዘዋውሮ እንደልቡ ሰርቶና ኑሮ መስርቶ እንዳይኖር የቋንቋንና ሌሎችንም ግርዶሾች አበጅቶ፣ አንዱ ጎሳ ከሌላው ጋር የጎሪጥ እንዲተያይ በማድረግ መራራቅ እየሰፋና የአንድ አገራዊነት ስሜት እየቀዘቀዘ እንዲሄድ እያደረገ እንደሆነ ግልጽ ነው። ሄህ ሁኔታ እንዲቀጥል ማድረግ ደግሞ ወደፊት የሚያስከትለውን መጠነ ሰፊ አደጋ ካሁኑ አለመገመት አንድም አላዋቂነት ወይም አውቆ አጥፊነት ነው። ዛሬ በተዘረጋው ሥርዓት የሰው ህልውና በዘር መስፈርት የሚታመስ በመሆኑ፣ መቀራራብን ሳይሆን መራራቅን፣ ከዚያም አልፎ እንዲያውም ቀደም ብሎ ተመስርተው የነበሩ የትዳር፣ የተላያዩ ህብረተሰባዊ ትስስሮች ፈርሰው የብዙ ቤተሰብ መበታተን እንደደረሰ የሚታወቅ ነው። በወተር፣ በበደኖ፣ በአርሲ-አርባጉጉ ወዘተ የተፈጸሙትንና ዛሬም በየካባቢው የሚፈሙትን በተለያዩ ጎሳዎች መካከል የሚካሄዱ ግጭቶች፣ በቀጥታ መንግሥትን በመሳሪያ በሚፋለሙት ሃይሎችና በመንግሥት ወታደሮች መካከል የሚካሄደው ፍልሚያ፣ ባጠቃላይም ዛሬ

እንደሚባለው የገዥው ጎሳ ከመጣበት አካባቢ በስተቀር -እስከመቼ እንደሚቆይ ባይታወቅም -ጥይት የማይጮህበት፣ አካባቢ እንደሌለ ሁሉ፣ ሁኔታውም በየትኛውም ጊዜና ቦታ ይሁን በምንም፣ መመዘኛ የጠብ እንጂ የጤና ምልክት ሆኖ አያውቅም።

የኦሮሞ ህዝብ ነጻነት ግንባርን ሁኔታ ስንመልከት አቶ መለሰ እንደሚሉት አሸባሪ እየቀጣን ነው ባይ ናቸው። በሻቢያ እየሰለጠነ ነውም ይላሉ፣ በማንም ሰለጠነ አልሰለጠነ ጉዳዩ ከቁጥር የሚገባ አይደለም፣ ለመሆኑስ ሻቢያ ያሳሰለጠነው ማን አለና ነው? ለዚህ ጉዳይ ዋቢ ካቶ መለስና ከወያኔ ሰዎች የበለጠ ምስክር ፍለጋ መሄድ የጫማ ሶል መጨረስ ነው። በርግጥ በሻቢያ የተረዱ፣ ሁሉ በለስ ቀንታቸዋለች ባንልም። ቀድሞ የሃይለ ሥላሴ መንግሥት ጀብሃንና ሻቢያን ሽፍቶች፣ ወንበዴዎች፣ ሲል፣ ደርግም ሻቢያንና ወያኔን እንደዚሁ በአረብ አገሮች የሚረዱ ወንበዴዎች እያለ አንቦ ሲደርሱ ሁሉ ሲያላዝን እንደቆየ ስለምናውቀው አቶ መለስም ከዚህ የተለየ ቅኝት እያሰሙን አይደለም። እዚህ ላይ በጣም ልብ ማለት የሚገባን ነገር ቢኖር ደግሞ ወያኔ ሲፈረካከስ በአቶ መለስ እንደ ሸክላ ተጠፍጥፈው የተሰሩትም ተለጣፊዎችም አብረው ሲፈረካከሱ፣ በኦፒዲዮነት ከሚታወቀው ጥፍጥፍ የመለስ አገልጋዮች እየፈለሱ (እየከዱ ) ሲወጡ ሌላ ድርጅት እናቁዋቅም፣ ወይም ሌላ በሀገር ውስጥ የሚገኝ ደርጅት እንግባ አላሉም። ሁሉም እየበረሩ ያረፉት ኦነግ ላይ ነው። ይህ የሚያሳየው ኦፒዲዮን ታማኝ ሎሌ ለማድረግ እንደማይቻል፣ በተያያዥም የኦሮሞን ህዝብ ለማኅበት አስቸጋሪ እንደሚሆንና በመፈናከቱም በኩል ቢሆን፣ በየቴሌቪዥኑ ይህን ያህል የኦኤልፍ ተዋጊ ማርከናል እየተባለ የሚለፈፈው፣ ምርኮኛው እውነትም ይሁን አይሁን "ውስጡን ለቄስ" እንበልና፣ ሰለምርኮኛ የሚወራው ጦርነት ባለበት ጊዜ ስለሆነ፣ ነገም በወዲያ በኩል እንዲሁ ከመለስ ወታደር የተማረከ ቢለን አንሰማም አንልም መችም። በደቡብ የጎሳ ግቶችም በኩል የሚታየውና የሚሰማው ትርምስ የታማኝ ሎሌነትን ጥያቄ ውስጥ ከማስገባት የተለየ መልዕክት አይኖረውም። እስካሁን ጸጥ ለጥ ብሎ ስለምኑም ስለምናምኑም ሳይሰማ በታማኝ አገልጋይነት አለ የሚባለው ጥቁር ነጥብ ያልታየበት ካማራው የተመለመለው ተለጣፊ ሲሆን፣ ይህም ሊሆን የቻለው የተለጣፊውን ድርጅት አመራር የጨበጡት ሰዎች ከላይ/ከሰማይ እንደበረከት ዓይነት የተሰጡት ሰዎች በመሆናቸው ነው በሚል ድምዳሜ ነው ታዛቢው ግምገማውን የሚቋጨው። ይህም ጠብ ከሚባል በስተቀር በሌላ ስም ክርስትና ሊነሳ አይችልም።

ሌላም አለ። በ 98 በመቶ የፓርላማ መቀመጫዎችን ባሸነፈ ፓርቲ የተመረጡት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ወደአውሮፕላን ጣቢያ ... ወዘተ ለመሄድ ሲፈልጉ፣ የሳቸው መኪና የሚያልፍበት መንገድ ዳርቻ ሰው አልባ መሆን እንዳለበት፣ ለስራ ጉዳይም ውጭ የሚገኘው ሰው ከዋናው መንገድ ዞር ብሎ በሚገኙ ጥቃቅን የግር መንገዶችና መሿለኪያዎች አቅጣጫ እንዲይዝ፣ ፊቱን አዙሮ ጀርባውን ለጠቅላይ ሚንስትሩ ሰጥቶ እንዲቆም ይደረጋል፣ ይህ ጠብ ካልተባለ ምን እንደሚባል ይነገረን፣ ባዮች ነን።

እንቀጥል፣ በደርግ የመጨረሻ ዘመን አካባቢ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጥላቻ ብሶቱ ያወጣው መፈክር "የፈለገው ይሁን፣ የፈለገው ይምጣ፣ ከደርግ የከፋ ከደርግ የባሰ አይመጣም የሚል ነበር።" ዛሬ ግን የደረሰው መፈክር "ከዚህ ይብስ አያምጣ" ሆኗል። ይህ በጣም የከፋ ነገር ነው። ሕዝብ የፖለቲካውን መስክ ገሸሽ አድርጎ ተጨባጭ ነገር ወደማይ ጠይቀው ወደ ሃይማኖት መስክ ተሰማርቶ ችግሩን ሁሉ አውጥቶና አውርዶ ለተቀበለው አምላኩ እያቀረበ ነው። በተለይ ደግሞ በዚህ መስክ ለተሰማራው ምሁር ፣

"የሚያስበው በሆድ
መዋያው ቤተክርስቲያንና
መስጊድ።"

የምትል ስንኝ ተቋዋጥሮለት፣ የሚቀለድበት ክፍል የሆነበት ሰዓት ላይ ነው የምንገኘው። በየመስጊዱ፣ በየቤተክርስቲያኑ አንተው ያመጣኸውን አንተው በኪነጥበብህ ውሰድልን እያለ መለማመኑን እያቀለጠው ነው። ይህም ራሱን የቻለ ጠብ ነው።

ሌላም መደምደሚያ አለ፣ መናልባትም ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸውን ሳንጠቅስም በራሱ በቂ የሚሆን። እስከዛሬ ያልታየና ያልተሰማ ነገር። "ኢትዮጵያዊ መሪ የለኝም" በማለት የመሪዎቹን ኢትዮጵያዊነት የኢትዮጵያ ህዝብ ጥያቄ ውስጥ ያስገባበት ጊዜ የመለስ ዜናዊ ያስተዳደር ዘመን መሁኑ ነው። ይህ ደግሞ የጠቦች ሁሉ ቁንጮ ሆኖ የሚቀርብ ነው። በጣም አስከፊ ነው። ገዥውንም ተገዥውንም የሚያሳፍር ነው።

መቼም በኢትዮጵያ ውስጥ ላለው ጡብ ጡብ መሽተት ሁኔታ መረጃዎችን በሙሉ እንዘርዝር ካልን ቀናትና ዓመታትም ስለማይበቁ እነዚሁኑ ለፍሬ አያብቃቸው እያልን፣

እኛ እርቅ ስንል እንግዲህ እነዚህ ሁሉ ከላይ የዘረዘርናቸውና ሌሎችም ገና በየጊዜው በዚሁ ዝርዝር ውስጥ ለመጠቃለል የሚችሉ ትርምሶች ተካብተው፣ ተካብተው፣ ወደ እርስ በርስ መጠፋፋቱ ተዛውረው ብዙ ድልድዮች ፈርሰው፣ ባንኮች ተዘርፈው፣ ሰዎች ከመኖሪያ ቀያቸው ተፈናቅለው ብዙ ለልማት የሚውሉ ሪሶርሶች (የሃብት ምንጮች) ለርስ በርሱ ጦርነት ማስተናገጃ ከመሆናቸው ተርፈው፣ አንዱ ትግሬ ሌላውን ትግሬ ፣ አንዱ ኦሮሞ ሌላውን ኦሮሞ ፣ አንዱ አማራ ሌላውን አማራ፣ አንዱ ሃድያ ሌላውን ሃድያ ... ወዘተ አጥፍቶ ጀግና ተብሎ ሃውልት የሚሰራለት፣ - ለምሳሌ ትግራይ ውስጥ የተገነባው የሰማእታት መታሰቢ የሚባለው አርባ ሺህ የትግሬ ሰው በአቶ መለስ አሰላፊነት ኤርትራን ለማስገንጠልና የኢትዮጵያን አንድነት ለማቃወስ ሲታገል ያለቀውን ለማስታወስ ነው። ግን እኮ ለኢትዮጵያ አንድነት መከበር፣ አገር አላስገነጥልም ብሎ በመንግሥት ወገን ተሰልፎ ያለቀም የትግሬ ሰው ብዙ ነው። የነዚህኞቹ ትግሬዎች እናትም ለሞቱባት ልጆችዋ ሃውልት ቢሰራላቸው እንደማይጠላት፣ -ከሆነ እንዲያውም ወግ የሚኖረው ይሄኛው ሳይሆን ይቀራል? - እርግጠኛ ነን። ለብሄራዊ እርቅ ፈላጊዎች ግን የ "ሰማእታት" ግንቡ የጡብ፣ ምልክት ስለሆነ መፍረስ አለበት፣ ነው። የምንለው።

ችግሮቻችንን ለመፍታት ጡበመንጃ የሚለውን የባህላዊ አሰራራችን ማተብ እንበጥስና፣ ሌላ ተወያይቶ ችግርን መፍታት የሚል ማተብ አጥልቀን፣ አቶ መለስ ያማራን የአገዛዝ ጭቆና ለመታገል ገስግሰው ጫካ እንደገቡት፣ ዛሬ ደግሞ የትግሬን የአገዛዝ ጭቆና ለመታገል ሌላው በተራው ክቡርነታቸው እንዳሉት ጨርቁን መንገድ ያድርግልህ ተብሎ እሳቸው ጥለውት ወደመጡበት ጫካ አይሸኝ፣ የተሸኘውም ይመለስና ጠረጴዛ ከቦ ይቀመጥ ማለታችን ነው።

ቀደም ሲል እንደጠቀስነው ስልጣን ባቁዋራጭ ፍለጋ የሚባለውም "ዶሮ ብታልም ጥሬዋን" እንዲሉ ካልሆነ በስተቀር የብሔራዊ እርቅ ጠያቂዎች ስልጣን ባቁዋራጭ ላጥ ለማድረግ ሳይሆን፣ ባቁዋራጭ የተያዘው ይለቀቅና በወግ በማዕረግ ይያዝ ነው የምንለው። ከቡርነታቸው ያልሆ ኑትን ሆነው - አረብ ነኝ ያሉትን እንዳይረሱ ለማስታወስ ነው - ሥልጣን ከመንግሥቱ ሃይለ ማርያም እንደነጠቁት ሁሉ አንዱ ነፍሰበላ ነጥቆአቸው እንደገና ሌላ አዲስ የመከራ ዙር እንዳያስጀምረን ለመከላከልም ነው።

እዚህ ላይ ግን ከምንም ባላነሰ ሊጤን የሚገባው ጉዳይ፣ በብሄራዊ ዕርቅ አማካይነት የሃሳብ ልዩነት የሌለበት፣ የሃሳብ ግጭት የማይኖርበት "የመላዕክት" ስብስብ የሰፈነበት ዓለም እንፍጠር ማለታችን ነው ተብሎ ለውንጀላ እንዳንዳረግ ያስፈልጋል፣ የሃሳብ ልዩነትና የሃሳብ ግጭጥ ምንጊዜም ይኖራል። ይህ የሌለበት ሁብረተሰብም ሊታሰብ የሚቻል አይደለም። ከሊቃውንት እንደሚሰማ ውም "የዴሞክራሲ -አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሳይሆን- ህልውና የሚጠበቀው በሃሳብ ልዩነትና በሃሳብ ግጭት ነው" ይላሉ፣ የኛም የብሄራዊ እርቅ ጥያቄ አራማጆች ምኞትም ሆነ ፍላጎት ከዚህ መርህ ፈቀቅ የሚል አይደለም። ጥሪያችንም የሃሳብ ልዩነቶችና የሃሳብ ግጭቶች እየኖሩ ሄደው ካንዱ የጥፋት ተራራ ወደሌላው በመዛመት፣ ማለቂያ የሌለው የጥፋት አዙሪት ውስጥ እንዲከቱን መደረጉ ቀርቶ፣ ውጤታቸው ወደጥፋት ሳይሆን ወደ ልማት፣ ወደድቀት ሳይሆን ወደእድገት እንዲያመራ መሆን አለበት፣ ነው።

ለዚህም የብሄራዊ እርቁ የመጨረሻ መቋጫ፣ አንድ ሃይለኛ በጉልበቱ ስልጣን በያዘ ቁጥር እየቀደደ በራሱ ሽንጥ እየለካ የሚሰፋውና ሌላው እንዲያጠልቀው የሚደረግ "ሕገመንግሥት" ሳይሆን፣" የህብረተሰቡ ነጻና ፍተሃዊ አስተሳሰብ የተንጸባረቀበትና የጋራ ስምምነት የተደረሰበት፣ የሃሳብ ልዩነቶችና የሃሳብ ግጭቶች በጥሞና የሚስተናገዱበት፣ በተወሰነ ዘመን በሚካሄድ ጠቅላላ ሕዝባዊ ምርጫ አስተ ዳደሩን የሚረከበው ሃይል በጥንቃቄ እንደሚጠብቀው ቃለ-መሃላ ፈጽሞ የሚረከበው ሕገመንግስት መፈጠር ይሆናል፣ ብሄራዊ እርቅ ስንልም ከዚህ ያነሰም ሆነ፣ የበዛም መድረሻ ታይቶን አይደለም።